# ፋሲካ (ትንሣዔ)

**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**

nigatuasteraye@yahoo.com

**ግንቦት ፳፻፫ ዓ.ም.**

**ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::**

http://www.medhanialemeotcks.org/

# መግቢያ

በጾማችን ወቅት ቅበላ በሚል ርዕስ **"ቅበላ የጾም መግቢያ ብቻ አይደለም፡፡ የሕይወትና የታሪክ ጉዞ መግቢያ በርም ነው"** በማለት በስድስት አንቀጾች ያቀረብኳትን ጦማር ያነበባችሁ ወገኖቼ፥ በጦማሯ መርካታችሁን ገልጻችሁ፥ በፋሲካው አመታዊ በአልም የሚሰማህን እንድታካፍለን ተስፋ አለን ባላችሁኝ መሠረት፥ የዘንድሮውን ፋሲካ በመንተራስ፥ ከፋሲካው በዓል ጋራ የተያያዙትን ሞትን መቃብርን ትንሣኤንና ለነዚህስ ምስክሩ ማነው? በሚሉ አናቅጽ ከፍየ፥ *'አፈር ብላ'* የሚለውን ባሕላዊ ምሬታችንን መደምደሚያ በማድረግ ይህችን ጦማር አቀርባለሁ:: በነገራችን ላይ ከትንሳዔ ዕለት ጀምሮ እስከ **በዓል ፶ (ጰራቅሊጦስ)** ማለትም ሰኔ ፭ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም. ድረስ ሰሙነ-ፋሲካ ይባል:: ስለ ጰራቅሊጦስ ከዚህ በፊት የጻፍኳትን ጦማር ይህን http://www.medhanialemeotcks.org/pdf/Peraklitos%20teglebete%20final.pdf

**፩ኛ. ሞት**

**፪ኛ. መቃብር**

**፫ኛ. ትንሣዔ**

**፬ኛ. ማነው ምስክሩ?**

**፭ኛ. "አፈር ብላ"**

# መቅድም

"እንስሳት እለ በሙ ሕምዝ ወዘከመ አራዊት መፃጥያን እለ በሙ ፅፍራት ወመጉረጽ አስናን ወእለ ይሴሰዩ ሕምዛተ ወበቁላተኒ እለ ያማስንዎ ለልብ ወለኩሉ ሥጋ በበሊያቱ"(ፍ. አን ፳፫፡ ቁጥ ፰፻፯):: ማለትም፡- "አንቀው ጨምድደው በሚይዙ ረዣዥም ጥፍሮቻቸው፥ ቆራርጠውና ከታትፈው በሚያደቁ ጥርሶቻቸው ያገኙቱን ሁሉ እያደኑ የሚበሉ እንስሳት ርኩሳን ናቸው፥ አትብሏቸው፥ መርዝ አላቸው::" ከተባሉት አራዊት የተገለበጡትን የአረማውያን ባሕርያት እርሾ ከውስጣችን አውጥተን ግብዝነት በራቀው ሰላም፥ ፍቅር፥ ርኅራኄና ትህትና እርስ በርሳችን ተቀባብለን፥ ቅበላ ጾማችን ለምንደመድምበት ለፋሲካው (ትንሳዔ) በዓል እንደሚያዘጋጀን ገልጬ ነበር::

ጾሙን ፈጽመን ፋሲካን (ትንሣዔን) ስናከብር ደግሞ "ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ" ማለትም፡- ሰው ይቅርና ምድርም በክርስቶስ ደም በመታጠቧ የፋሲካውን በዓል ታከብራለች" የሚለውን በመዘመር፥ በክርስቶስ ደም በጸዳው ኅሊናችን፥ በቅንነት በጸዳው አዕምሮሯችን በእውነት በተኳለው ዓይነ ሕሊናችን ከሞት በኋላ የሚጠብቀንን ሕይወት አሻግረን መመልከት መቻላችንንና፥ በአራዊት ጠባይ በተመረዙ አረመኔዎች እጅ ለወደቁት፡ ተስፋ ለቆረጡት፡ የሕይወት ብርሃን የሞራል የመንፈስ ልዕልና ትንሣኤ መሆኑን ለምንሰጠው ምስክርነት ምንጭ ነው::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ወኩሉ ሰብእ በበ ሥርአቱ" (፩ኛ ቆሮ ፲፭፡፳፫):: እንዳለው አማኝም ይሁን የማያምን (Atheist) ነኝ የሚልም፥ በተወሰነለት ሰከንድ ይሕችን ዓለም በሞት እስኪሰናበታት ድረስ፥ በግሉም ከኅብረተ ሰቡ ጋርም የሚጋራው ትንግርት በሕይወቱ ቢያንስ አንድ ቀን ሳይገጥመው አይቀርም:: በግልና በጋራ የሚደርሱት አዳዲስ ትንግርቶች ጥቅጥቅ ባለ ጫካ በቅለው ተራርቀው በቆሙ ዛፎች ላይ እንደሚጠመጠሙ ሐረጎች፥ በወራት ርቀት ውስጥ ተፈናጥረው በሚከበሩት እንደፋሲካ (ትንሣኤ) በመሳሰሉት ታላላቅ በዓላት ላይ ይጠመጠማሉ::

የገጠማትን ትንግርት ስትጽፍ የኖረች እንደ ኢትዮጵያ ያለች አገር ትቅርና፥ ፊደል የሌላቸው አገሮችም፥ በወቅት እየተመሩ ከቦታ ወደ ሌላ ቦታ ከሚሄዱ ወፎች ይሻላሉና ባይጽፉና ባይመዘግቡም፥ ወቅቶችን በማንበብ ብቻ ሕይወታቸውን ይመራሉ:: John S Mbiti የተባሉ ስለ አፍሪካ ሃይማኖትና ፍልስፍና ያጠኑ ሰው "things are embraced within the Macro Time"(page 23) "ትንግርቶች እየተጠነጠነች በምትሽከረከረው ምንት-ሰዓት ላይ አንድ ላይ ይተቃቀፋሉ" እንዳሉት፥-ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ክርስቶስ ትንሣዔ ሲናገር "እስመ ተዘብሐ ለነ ፋሲካነ ክርስቶስ"(፩ኛ ቆሮ ፭፡፯) ያለው፥ በየዓመቱ እየተመላለሰ ሲከበር በኖረው ፋሲካ ላይ እየተደራረቡና እየተጠመጠሙ የቆዩትን ትዝታዎች ከአዲስ ኪዳኑ ትንግርት ጋራ ደምሮና ለይቶ ለማስቀመጥ ነው::

የፋሲካው በዓል ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ እየተተካካ የሚቀጥለውን ትውልድንና ዘመንን እየሰነጠቀ ሳያቋርጥ ተሳስሮ ሲከበር ይኖራል:: ተሳስረው ሲታሰቡ ከሚኖሩ ነገሮች አንዱ የዮሴፍ አጽም ነው:: "ወአምሐሎሙ ዮሴፍ ለደቂቀ እስራኤል ወይቤሎሙ አመ ይሔውጸክሙ እግዚአብሔር አውጽኡ አዕጽምትየ እምዝየ ምሴክሙ"(ዘፍ ፶፡፳፭) እንዲል፥ ማለትም፡-"እግዚአብሔር በምሕረቱ በጎበኛችሁ ጊዜ በፋሲካው

ትንግርት ስትወጡ አደራችሁን አጥንቴን  አትርሱብኝ” (ዘጸ ፲፫፡፲፱) ብሎ ዮሴፍ የተማጸነለት አጥንትና በወቅቱ አብረው የተከናወኑት ነገሮች ሁሉ፥ ከፋሲካው ትዝታ ጋራ የተሳሰሩ ናቸው:: ኤጲፋፍዮስ የሚባለው የቆጵሮሱ ኦርቶዶክሳዊ ሊቅ መልሕቅ በተባለው መጽሐፉ፥ ስለ ክርስቶስ ትንሳዔ ሲናገር፥ ሃይማኖት ታሪክና ባሕል የሚያገናኛቸውን አጥንቶች ሳይቀሩ አገናኝቶ ጠቅሷቸዋል::

በዓለም ዙሪያ ተበትነው የሚኖሩ ኦሪታውያን ኅብረተ ሰቦች፥ ፋሲካው ከተፈጸመበት ቀንና ሰዓት ጀምሮ እስካሁን እየተደራረቡ የሚገጥሟቸውን አዳዲስ ውጣ ውረዶች ሁሉ ለበዓሉ ማእከል ከሆነው ከፋሲካው ጋራ እያስተሳሰሩ የፋሲካን በዓል የታሪካቸው አምድ ምልክትና ማስታወሻ አድርገውታል::

የፋሲካው ታሪካዊ ማስተሳሰር በኦሪታውያን ብቻ ሳይወስን፥ “ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶልናል” ብለን የምናምን ክርስቲያኖችንንም ጠልፎ በመከተት የታሪኩ ገባር አድርጎናል:: ዮሴፍ የፋሲካውን ጉዞ ስትጀምሩ አጥንቴም አብሯችሁ እንዲጓዝ አድርጉልኝ እንዳለው፥ እኛም ለፋሲካው (ትንሣዔ) ማእከል የሆነውን ክርስቶስን ለማንገስ የፋሲካውን (የትንሣዔውን) እራት በከበብንበት በልጅነት ዘመን፥ ከፋሲካው ማእድ እየቆረሱ ያጎረሱንን እናት አባት፥ አብረውን የተሰለፉት ወገኖችንና የተሰለፍንባቸውን ቦታዎች እንዳንረሳቸው ይማጸኑናል:: ባለፈው አመት የነበሩ፥ ዘንድሮ በሞትም ሆነ በሕይወት አገር ለቀው ወደ ሌላ አገር በመሄድ የተለዩት ሁሉ የሚታወሱባቸው ናቸው:: በነዚህ አይነት በዓላት ቤተ ሰቦች በሞሰቡ ዙሪያ ሲቀመጡ፥ በሞትም ሆነ፥ ከፍቷቸው አገር ለቀው የተለዩ ወዳጅ ዘመድ አቀማመጥና እንቅስቃሴያቸው ሁሉ ተሳስሮ ይመጣባቸውና እንባቸውን እንዲያፈሱ ያደርጋቸዋል:: ለተወሰነ ደቂቃ የሐዘንና የትካዜ ደመና በሞሰቡ ላይ ያጠላበታል:: የታች አምናውን ትንሣኤ ያከበርንበት ስሜት ከአምናው የተለየ ነው::

ፋሲካም ሆነ ሌሎች በዓላትና ኢትዮጵያዊ ቅኔ ወይም ሥነ ጽሑፍ በየዘመኑና በየአካባቢው ለሚፈጸመው ሁሉ ትንግርት፥ የእለት ጽንሶች ናቸው ይላሉ አበው፤ የእለት ጽንስ በመጠንና በጥንካሬ እያደገ እየተለወጠ ለሚሄደው አካል መሠረት እንደሆነ፥ ባንድ ወቅትና አካባቢ የሚፈልቅ ቅኔም በፈለቀበት ወቅትና አካባቢ የተካሄደውን ከፍሎና አካቶ ለማንጸባርቅ አሠረ-ንጉሥ ወይም ለዓለም በሚል ፈሊጥ ከፍለውታል::

ከባለ ቅኔና ከጸሐፊ አዕምሮ የምትፈልቅ ሐረግ አካታ የምትይዘው ጽንሰ-አሳብ፥ ከዓመታትና ዘመናት በኋላ ለሚጽፉ ደራስያን የተከናወኑትን ተገጣጣሚወች በመጠኑም ቢሆን ማንጸባረቅ አለባት:: በዚህ አመት የምናከብረው ፋሲካም የዓባይ ወንዝ መገደብ ወሬ ተለጥፎበታል::

የዐባይ ውኀ ባንጠቀምበትም፥ ከልባችን ከሚፈልቀው ደማችን ጋራ መንታ ሆኖ ሲፈልቅ በመኖሩ ከቅኔያችን፥ ከስነ ጽሑፋችን፥ ከታሪካችን፥ ከባሕላችንና ከሁለመናችን ጋራ የተሳሰረ ነው:: ከኛ ተሸከሞ በሚወስደው ጸጋና ረድኤት እየረኩ፥ “ያባይን እናት ውሐ ጠማት” በማለት ከሚያፌዙብን ፌዝ ወጥተን፥ መሬታችን ከመራቆት፥ ከብቶቻችን ከድርቅ፥ ሕዝባችን ከጥማት መላቀቁን የማይናፍቅ ዜጋ ባይኖርም፥ ይህን የተቀደሰ አለማ የሚያወሩ ሰዎች፥ ተለጣፊ በሚል መርኋቸው ወርቅን በጠጠር፥ እጣንን በኩበት፥ ማርን በእሬት እየሸፈኑ በማቅረብ ያሰለቹ በመሆናቸው፥ ያባይን ግድብ መሸፈኛ አርገው የፈለጉትን ነገር ሊደብቁበት የፈጠሩት ሸፍጥ ነው እየተባለ ነው:: ሆኖም የኢትዮጵያውያንን መንፈስ ጎትተው ወደፈለጉበት አቅጣጫ ለመውሰድ መጎተቻ ገመድ አድርገው በዘንድሮው ፋሲካ ላይ ለጥፈው አቅርበውታልና፥ በዘንድሮው ፋሲካ ሰሞን ለምንቀኛቸውና ለምንጽፋቸው ነገሮች ሁሉ ተለጣፊ ሰም ሆኖ ቀርቧል::

ፋሲካ በኢትዮጵያ መታሰብና መከበር ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በደግና በክፉ ቀን ሳያቋርጥ በያመቱ እየተመላለሰ ሲመጣ እየነካና እየዳሰሰ ካሳለፋቸው ሰዎቻችንና በዚያው ወቅት ከተፈጸሙት ታሪካችን ጋራ ሁሉ ያገናኘናል:: በክፉ ዘመናት ለምሳሌ ዮዲት ለ፵ ዘመን ኢትዮጵያን ባቃጠለችበት ዘመን ፵ ጊዜ ሲከበር፥ በ፵ው ዘመን ሁሉ ከፍና ዝቅ እያለ በኢትዮጵያ ላይ የነደደው የመከራው ግለት ከመከበር አላቆመውም:: ፲፭ ጊዜ ኡደት ባደረገው በግራኝ ሞሐመድ ጊዜም  የፋሲካው በዓል ፲፭ ጊዜ ተከብሯል:: ጣሊያን አገር እያቃጠለ በቆየባቸው በ፭ አመታትም አልተቋረጠም:: ሰው ቀጥፎ በበላው በለስ ምክንያት ምድር በምታበቅላቸው እሾህና አሜከላ እየወጋች እንድትቀጣው የፈጣሪ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ፥ የተረጋጋና የሰላም ጊዜ በሚባለው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመንም እንኳ፥ እነ በላይ ዘለቀ በግፍ ተሰቅለዋል:: በደርግ ጊዜም በተለይ ከ፷፯ እስከ ፹፬ አመታት በተከበሩት የፋሲካ በዓላት ከጥቂት ሰዎችና ከደርግ አባላት ቤት በቀር በመላ ኢትዮጵያውያን ደጃፍ በበግ ፋንታ የሰው ጠቦቶች ታርደዋል:: በዚህ ዘመን የምናከብረው ፋሲካ ግን፥ ባለፉት መንግሥታት ዘመናት ውስጥ በብዙ ትዝታዎች ታጅበው ከተከበሩት ፋሲካዎች ጋራ ሲነጻጸር፥ ለ፳ አመታት ፳ ጊዜ እየተመላለሰ ያካበታቸው ትዝታዎች ከኢትዮጵያ መቆራረስና መቆራረጥ ጋራ ተሳስረው፥ ከሁሉም በላይ እጅግ ለከፋው ዘመን ማስታወሻ ሆኗል::

እግዚአብሔር የትናንቱ፥ የዛሬውና የነገው እንደሆነ ሁሉ፥ የቃሉ ብርሃን በተጻፈበት ዘመንና ትውልድ ላይ ብቻ እንዲያበራ የተወሰነ አይደለም:: እየተዛዘለና እየተቆላለፈ የሚመጣውን ትንግርት እየተለዋወጠ ለሚቀባበለው ትውልድ መተርጎም እንዲያስችል በሊቃውንት ዓይነ ሕሊና ላይ የተተከለ ዘላለማዊ የብርሃን ጎርፍ ነው:: እንደምናየው ይህ ዘመን ክፉ በመሆኑ፥ ሁላችንንም ተለዋዋጭና ተገለባባጭ ባህርይ እያጠቃን ነው:: በዚህ አይነት ተለዋዋጭ ባሕርይ የማይለዋወጠውን  የእግዚአብሔርን ቃል ተርጉሞና አብራርቶ በማቅረብ መመስከር አያስችልም:: የሚገለባበጥና አቋሙን የሚቀያይር ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል የሚተረጉም ከሆነማ "ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ፥ ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጅ ሞኞች አትሁኑ" (ኤፌ ፭፡፲፮):: ተብሎ የተነገረው ቃል ተረት ሆነ ማለት ነው:: የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩ ሰዎች በሚለዋወጡ ዓለማውያን መሪዎች ምኞትና ፈቃድ ከተቃኙ፥ ክፉውን ዘመን ሊዋጁ ይቅርና፥ እራሳቸው በክፉ ዘመን ተዋጅተው፥ የሚሰማቸውን ሁሉ እነሱ በተዋጁበት ክፉ ዘመን የሚያስዋጁ ይሆናሉ::

ፋሲካን (ትንሣዔን) የመሳሰሉ መንፈሳውያን በዓላት የሚታወሱባቸው ቀኖች፥ የዶሮ ሥጋ እንዲበላባቸው ወይን እንዲጠጣባቸው ከሌሎች ዕለታት የተለዩ አይደሉም:: ቀጣፊዎች እየቀጣጠፉ በሚቀይሱት የምጣኔ ሐብት ውስጥ የሚኖር ዜጋ በሚገጥመው የኑሮ ቀውስ ሥጋ መብላት ወይን መጠጣት ቢያቅተው፥ መጨነቅ ቀርቶ አያስበውም:: በዓላት የመንፈስ የነጻነትና የሞራል ልዕልና የሚመነጩባቸው፥ በቀጣፊዎችና በነፍጠኞች መካከል የተካሄዱት ትንቅንቆች የሚንጸባርቁባቸው ናቸው:: የበሰለ ዜጋ በዓሉ በተሸከማቸው በድል፥ በነጻነት፥ በሞራል ልዕልና መንፈስ ስሜታቸውንና መንፈሳቸውን ያረካሉ እንጅ፥ በዓሉን በመብልና በመጠጥ ብቻ አይተረጉሙትም::

የበዓሉን ምሥጢር በቤተ ክርስቲያን ከተሳተፍን በኋላ ከቤታችን ተመልሰን በማእድ ዙሪያ የነበረው ባሕላዊ ልምዳችን መቋረጥ፥ የግራኝ መሐመድን፥ የዮዲትንና የጣሊያን አመራር ገልብጦ የመጣ መሪ የፈጠረው ተለጣፊ አመራር ያስከተለው የኑሮ ቀውስ መሆኑን ያስገነዝበናል:: ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ "በሰማይና በምድር ድል ሥልጣን ተሰጠኝ" (ማቴ ፳፰፡፲፱) ባለው የድል አዋጅ ነጻነት የተጠማውን ስሜታችንን እናረካለን:: የድል ባለቤት የምንሆንባትን ቀን ጎሊናችን እንዲናፍቃት ያደርገናል::

ሕዝባዊ አካልነት የሌለው ተለጣፊ መንግስት፥ ተለጣፊ የሆነ ባእድ ነገር እያመጣ ውዝንብር የሚከት መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: ይልቁንስ በተለጣፊ ባህርዩ በዘንድሮው ፋሲካ በዓል ላይ ለጥፎ ያቀረበው የዐባይ ግድብ ወሬ፥ ስለ አገር፥ ስለ ወገን፥ ስለ ሃይማኖትና እውነት የሚገረፉትን፥ የሚደበደቡትን፥ የሚገደሉትንና የተቆራረሰችውን ኢትዮጵያ እንዳያዘናጋን መንቃት ይኖርብናል:: ኢትዮጵያውያን የሞት-ሞት ነው የሚሉት በሕዝብ ላይ ራሱን የለጠፈ መንግሥት በሚፈጥረው ተለጣፊ ወሬ እየተደናቆሩና እየተደናበሩ መኖርን ነው::

# ፩ኛ. ሞት

የሞትን ምሥጢር ለመግለጽ የኔ አቅም ይቅርና ዓለም ያፈራቻቸው ሊቃውንት ሰውን በተቀመጠበት የሚፈነግለውን እንቅልፍ ለመግለጽና ጨርሶ እንዳይመጣ ለማድረግ ካቅማቸው በላይ ነው:: ይሁን እንጅ የተነሣሁበት ርእስ ፋሲካ (ትንሣኤ) ከሞት ጋራ የተያያዘ ስለሆነ፡ ብዙ ሰዎች ስለሞት ከተናገሯቸው ብዙ ሐተታዎች ውስጥ፥ የኔን መንፈስ የነኩኝን ብቻ ጠቅሼ አባቶቻችን ሊቃውንት አበው ወደ ሚገልጹበት መንገድ እሻገራለሁ::

፩ኛ. Herman Hooker የተባለው ሰው "Death is as the foreshadowing of life. We die that we may die no more." በማለት ሞትን በሕይወት ላይ የተዘረጋ ጥላ አድርጎ፥ ሞት እንደገና ላለመሞት መሞት እንደሆነ ገለጸው::

፪ኛ. Sir. Oliver Lodge የተባለው ደግሞ "Death is not a foe, but an inevitable adventure" ማለትም፡- "ሞት ጠላት አይደለም:: ይልቁንም ባልተጠበቀ ሰዓት የሚፈጸም የማይቀር ነገር ነው" ብሎ ገለጸው::

፫ኛ. Tryon Edwards የተባለውም "Death has nothing terrible which life has not made so. A faithful Christian life in this world is the best preparation for next." ማለትም:- "ሞት በዚህ ዓለም ኑሮ ከሚገጥም ችግር የበለጠ የሚያስፈራ አይደለም:: ይልቁንም ሞት በክርስትና አምኖ በዚህ ዓለም ለሚኖር ክርስቲያን፥ ለሚቀጥለው ሕይወት በተሻለ መንገድ የሚያዘጋጅ ነው" ብሎታል:: "ሞትን ሳስብ ጭንቅላቴ ያበጠ እየመሰለኝ እራሴን እዳስሰዋለሁ" ብሎ ሴንትሉስ የሚኖር አንድ ኢትዮጵያዊ ወዳጄ የነገረኝንም ሳልጠቅስለት አላልፍም::

ነፍሳቸውን ይማርና አርቲስት ጥላሁን ገሠሠም:-

"ከመሞት አልድንም አትጠራጠሪ፥

*ሥጋየ ላንች ነው አታርጊኝ ብጣሪ"* በማለት ያንጎራጎሩት፥ የማይቀረውን ሞት ይቀራል ብሎ ከመዘናጋት ይልቅ፥ ኢትዮጵያዊነትን ሳያውቁ በመሪነት፥ የተዋሕዶ ሃይማኖትን ነገረ መለኮት ሳይረዱ በጳጳስነት በቄስነትና በመምህርነት መሰለፍ የታሪክ ብጣሪ መሆን፥ ከሞት እጅግ የከፋ መሆኑን የሚያስገንዝብ ነው::

ከግለ ሰቦች እይታ በተጨማሪም ሊቃውንት አበው ስለ ሞት በአንክሮና በተመስጦ ሲነጋገሩባቸው የሰማኋቸውን ጥቂቶችን ብጠቅስ መልካም ይመስለኛል:: ለምሳሌ "አ ሞት እፎ መሪር ዝክርከ ሶበ ትመጽእ ላእለ ብእሲ እንዘ ዳሕነ ይነብር፡ ወይዴለው በኵሉ ወቦ ኃይል ወፍቱሕ ነፍሱ ለበሊዕ" (ሲራ ፵፡፩):: የሚለውን ማለትም፡- "ልክበር ልበልጽግ ልብላ ልጠጣ ልድመቅ ላጊጥ በሚል መንፈስ ሰክሮ ሲከንፍ ሞት የሚደርስበት ሰው ሲታሰብ ምንኛ የሚዘገንን የሞት ሞት ነው?" ይባባሉ ነበር::

"ኢይክል ሰብዕ ረኪበ ኀቡረ ዘተገብረ መትሕተ ጸሐይ እመ ሚ መጠነ ይቤ ጠቢብ ከመ ያእምር" (መክ ፲፡፲፯):: ማለትም "ሰው ከጸሐይ በታች ያለውን ሁሉ አውቃለሁ ቢልም፥ ብዙ የማያውቀው ነገር አለው:: ከብዙው ውስጥም አንዱ ሞትን ነው" ይላሉ:: "ድንጋጼ ይእቲ ወፍርሀተ ልብ ትዝሕብታ ለዕለተ ሞት ሳዕለ ኵሉ እጓለ እመሕያው"(ሲራ ፵፡፪):: እንዷል፡- ሰው ምሥጢሩን ማወቅ ባይችልም ሞቱን የሚረሳ ከሆነ እጅግ የሚያስደነግጥና የሚያሰፈራ ነው" ይሉ ነበር:: ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አንዱ ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል የሚባሉት ባለ ቅኔም "ዓለም እስከ ጊዜሃ፡ በሐብለ ዝንጋኤ ትስሕበነ ወታውርደነ ታህተ፥ ኀበ ዘቀዳሚ መርገም" ብለው ተቀኝተዋል:: ሞትን የንግግራቸው ባለቤት ባያደርጉትም፥ የምንኖርባት ዓለም ሞትን አስረስተው ከደመና በታች የሚቀር ነገር እንድንሰራ የሚያደርጉ አሳሳቾች እንደምታፈራ ነግረውናል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፥ በዓለማችን ያሉት ታላላቅ እምነቶች የሚጋሩትን መጽሐፍ መሠረት በማድረግ ስለሞት ምን ብለው እንዳስተማሩን ከዚህ በታች እንመልከት:: ሞትን ለመግለጽ ከኦሪቱ መጽሐፍ ሶስት ጥቅሶችን መሠረት ያደርጋሉ::

፩ኛ "ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአርዌ ምድር እስመ ገበርኮ ለዝንቱ ግብር ርጉመ ኩን እምኵሉ እንስሳ ወእም ኵሉ አራዊተ ምድር "ወበእንግድዓከ ሑር ወመሬተ ትበልዕ" (ዘፍ ፫፥፲፬):: ማለትም፡- "ከእንስሳትና ከምድር አራዊት ሁሉ ተለይተህ የተረገምክ ሁን፥ በደረትህ ሂድ፡ አፈርም ብላ" ብሎ እግዚአብሔር እባብን የረገመበት ቃል ነው::

፪ኛ "ርግምተ ትኩን ምድር" (ዘፍ ፫፡፲፯):: ማለትም፡- "ምድርም የተረገመች ትሁን" ብሎ እግዚአብሔር ምድርን የረገመበት ቃል ነው::

፫ኛ. "ትገብእ ውስተ መሬት እንተ እምኔሃ ወጻእከ እስመ መሬት አንተ 'ወውስተ መሬት ትገብዕ' (ዘፍ ፫፡፲፱) ማለትም፡- "ወደመጣህባት መሬት ተመለስ" ብሎ እግዚአብሔር ሰውን የገሰጸበት ቃል ነው::ሊቃውንት አበው እነዚህን ከመጽሐፉ መዝዘው ካወጧቸው በኋላ፥ በምድርና በእባቡ ላይ የወደቀውን ባንድ ወገን ያደርጉና መለኮታዊ መርገም ብለው፥ በሰው ላይ የወደቀውን ግን በእባቡና በመሬት ላይ ከወደቀው መርገም በመለየት መለኮታዊ ተግሳጽ ይሉታል::

የብሉይ ሊቃውንት አበው እንደሚሉት፥ በእባቡና በመሬት ላይ የወደቀው የእግዚአብሔር ቃለ-መርገም ቀጥታ በሰው ላይ ቢሰነዘርበት ኖሮ፥ ጨርሶ ከመጥፋት በቀር "ናሁ አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ"( ዘፍ ፫፡፳፪) ማለትም፡- "አዳም ከኛ እንደአንዱ ሆነ" ተብሎ በመጀመሪያው አዳም ምትክ፥ የሕይወት በር መግቢያ የሚሆን ሌላ አዳም መጥቶ የሚታደግበት ተስፋ አይታቀድለትም ነበር::

"ቅንይዋ ለምድር ወኮንንዋሙ ለዓሣተ ባሕር ወለአራዊተ ምድር ወለእዋፈ ሰማይ ወለኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር"(ዘፍ ፩፥፳፰):: ማለትም፡- ሰው በባህር በየብስና በአየር ያለውን ሁሉ ፍጥረት እንዲገዛ ክቡር ሆኖ

ተፈጥሮ ሳለ፥ እንደገኘነቱ ክብሩን ጠብቆ ባለመገኘቱ ከእባቡ በታች ወደቀ:: እባቡ የሚልሰው፥ የሚበላውና በደረቱ የሚሳብብት አፈር ትቢያ ሆነ::

ሰው ጊዜው ደርሶለት ክርስቶስ መርቆና ከፍቶ በሰጠው ትንሣኤ እስኪነሳ ድረስ፥ ከሱ በታች የሆነው ፍጥረት እንዲልሰውና በደረቱ እንዲንከባለልበት ቢቀጣም፥ የማይለዋወጠው አምላክ "እንደ ምሳሌያችን ሰውን እንፍጠር" ብሎ አክብሮ የፈጠረበትን የመጀመሪያውን እቅድ በማፍረስ ወድቆ እንዲቀር አልተወውም:: መጀመሪያ በተነገረው ቃሉና፥ ባቀደው እቅዱ መሠረት "ናሁ አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ" (ዘፍ ፫፡፳፪) ብሎ ወደቀደመ ክብሩ የሚመለስበትን ተስፋ ወዲያውኑ ዘረጋለት::

ይሁን እንጅ እግዚአብሔርም "ከኛ እንዳንዱ ሆነ" ብሎ ለሰው በሰጠው ተስፋ ወልድ በተለየ አካሉ ከሰዎች መካከልም እንዳንዱ ሆኖ የሞትን ኃይል ደምስሶ እስኪነሳ ድረስ፥ መለኮትን ጸንሳ የወለደች እመቤታችን እንኳ ሳትቀር፥ ያዳም ልጅ ሁሉ "እስመ ኵልነ ደቂቀ አዳም ንሕነ፥ በእንተ ዝ ንመውት በእንተ አዳም አቡነ" (መቃ ካልዕ ፲፰፡፯) በአባታችን በአዳም ስሕተት ምክንያት ከሞት ጊዜአዊ ወጥመድ አላመለጠም::

ይህን ተመልክቶ ሊቁ አትናቴዎስ "ሰብሰ እንዘ ክቡር፥ እንዘ ንጉሥ፥ እንዘ ባዕል ውእቱ ኢያእመረ፥ ኮነ ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ፡ አሕሰረ ርእሶ አንደየ ርእሰ በሥምረተ አርኀበ ከርሶ ወአጽምአ ነፍሶ. . .እንዘ ልቡሰ ውእቱ ልብሰ ብርሃን አዕረቀ ሥጋሁ ወተከድነ አዕዳለ ዘማዕስ፥ (አትና ፪፻፲፯፡ ቁጥ ፳-፳፪፡ ፳፮፡ ፳፯):: እያለ ተናገረ:: ማለትም፡- <u>"ሰው ተፈጥሮን አክብሮ የሚከብር፥ እውነትን አንግሦ የሚነግሥ ባለጸጋ ነበር:: ነገር ግን ይህን ኃላፊነት ሊወጣ ይቅርና እርስ በርሱ የሚጠፋፋ እንስሳ ሆነ:: ከሰውነት ወርዶ ለመጠፋፋት ወደ እንስሳነት መቀየር ሌላው የሞት ሞት ነው"</u>::

<u>እንግዲህ ሰው ሞተ የሚባለው፥ በግልጽ ተነግሮት ካወቀው ህሊናውም ካረጋገጠው እውነት ፈርጥጦ፥ የገዛ ሕሊናው በሚፈርድበት ስሕተት ውስጥ ሲገባ፥ ጸጋውንና ክብሩን በፈቃዱ አዋርዶ የመንፈስና የጸጋ ረሐብተኛ ሲሆን፥ በቀጠፋት እጸበለስ ቅጠል ራሱን ከፍኖ ሲቀብርና፥ በተፈጥሮ እጅግ ዝቅተኛ ከሆነው እባብ በታች ወድቆ፥ እባቡ የሚልሰውና በደረቱ የሚሳብበት አፈር ትቢያ ሲሆን ነው</u>::

# ፪ኛ. መቃብር

"ወተኀብኡ አዳም ወብእሲቱ እምቅድመ እግዚአብሔር ማእከለ ዕጸዊሃ ለገነት . . . . ሰማእኩ ቃለከ እንዘ ታንሶሱ ውስተ ገነት ወፈራህኩ እስመ እራቅየ አነ ወተኀባዕኩ"(ዘፍ ፫፡፰-፲):: አዳምና ሄዋን የእጸበለስን ቅጠል ቀጥፈው ከበሉ በኋላ መራቆታቸውን ሲያውቁ ፈሩ፥ አፈሩና በቀጠፏት ቅጠል ራሳቸውን ጠቅልለው በገነት እጸዋት መካከል ተደበቁ:: ለተደበቁበት ምክንያት አዳም ለፈጣሪው የሰጠው መልስ "ድምጽህን ሰምቼ ፈራሁ ራቁቴን በመሆኔም በገነት ተደበቅሁ" የሚል ነው:: ኅሊና የሚያውቀውን እውነት ባለመፈጸም የተሰራችው ስሕተት (የቀጠፍናት ነገር) እራሷንመደበቂያ እንዲያደርጋት ሰውን ታታልለዋለች:: እግዚአብሔር ግን ሰው ንስሐ እንዲገባ እንጅ በቀጠፋት ቅጠል (ስሕተት) ለመደበቅ የሚያደርገውን ሙከራ አይቀበለውም:: "ትገብእ ውስተ መሬት እንተ እምኔሃ ወጻእከ እስመ መሬት አንተ <u>ወውስተ መሬት ትገብዕ</u>" (ዘፍ ፫፡፲፱) አለ:: ማለትም፡-

መደበቅን መቀበርን ከፈለግህ የምትደበቀብት የምትቀበረበት በራስህ ምርጫ ፍሬዋን ቀጥፈህ በበላህት ቅጠል አይደለም፥ ብሎ መጀመሪያ ወደ መጣበት ወደ አፈር ተመልሶ የመጨረሻ አስፈሪ በሆነው አፈር ለረዥም ዘመን እንዲደበቅ አዘዘው:: (ፈረንጆች ልጆቻቸው ሲያጠፉ time out ብለው በተለየ ጓዳ አስገብተው እንደሚዘጉባቸው ማለት ነው)::

መቃብር ነፍስና ሥጋ ሲለያዩ ሥጋ የሚቀበርበት ቦታ ብቻ አይደለም:: ሰው ስሕተት መሆኑን እያወቀ እግዚአብሔር አያየኝም፣ ሰውም አይደርስብኝም፣ ብሎ ተደብቆ ክፉ ነገር መሥራት የራሱን ጸጋ በራሱ ገፎ እራሱን በራሱ በቁም መቅበር ነው:: "እስመ ኵሉ ዘእኩይ ምግባሩ ይጸልእ ብርሃነ ወኢይመጽእ ኀበ ብርሃን ከመ ኢይትከሰቶ መግባሩ" (ዮሐንስ ፫) ሥራው ክፉ የሆነ ሁሉ ብርሃንን (ግልጥነት) ይጠላል:: ራሱን በጨለማ ገንዞ ትንሽም ትልቅም የቀጠፈ የሰረቀ በራሱ ሕሊና ዳኝነት፥ ቤቱንና አካባቢውን ሳይቀር ወደ ወህኒ ቤት ይቀይራል፡፡

የሕዝቡን ድምጽ ዘርፎና ሰርቆ ቀጥፎ የሕዝቡን በረከትና ፈቃድ ሳያገኝ ዘሎ ወደ ቤተ መንግሥት የሚገባም፥ የጽድቅ የምሕረት የጥበብ ምንጭ ነው ተብሎ የሚገመተው ቤተ መንግሥት ወደ መቃብርነት ይለወጥበታል:: በዚህ መንገድ ሥልጣን የጨበው መንግሥትም "እስመ ዓለም ያፈቅር እሊአሁ" እንደተባለው በቅጥፈት በውሸት የሚመስሉትን ይሰበስብበታል:: በዙሪያው የሚያሰልፈው ወታደር ሕዝባዊ መሆኑ ቀርቶ፥ ዘርፎ ለገባ፣ ነጻነትና የሕሊና መረጋጋት ለሌለው የሰረቀውን ሕዝብ ለማያምን መሪ ዘበኛ ይሆናል:: በዚህ አይነት መዋቅር የሚመራ ወታደራዊ ሠራዊት የደረቀ ሬሳ ተሸክሞ የሚሄድ ደምና ሕይወት የሌለው ጉንዳን ይሆናል::

"አምረው የሚታዩ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮች ናቸው"(ማቴ ፳፫፡፳፯) እንደተባለው፡- ጀኔራሎች ኮረኔሎች፥ ሻለቆች፥ ሌሎችም በዚህ አይነት መንግሥት የሚሰየሙ የቅጥፈት ተካፋዮች ሁሉ ደብቀው ሸፍነውና ጋርደው የተሸከሙት መሪ፥ በኃጢአቱ፥ በበደሉ በስብሶና ከርፍቶ በሚመራው ዜጋ መካከል የተጋደመ ሬሳ ነው:: ቤተ መንግሥቱም ሬሳ የተቀበረበት መቃብር ነው:: የለበሱት ልብስ ለነሱ የማእረግና የስልጣን ዩኒፎርም ቢመስላቸውም፥ ለጠቅላላ ሕዝብ ግን ከል የተነከረ የሐዘን ልብስ ነው::የሚጫኑበት መኪና የሬሳ ነው:: ድምጻቸውም የጻእር መጓጉር ነው::

"በመቃብር ሥጋችን እንደ ሰም ቀለጠች ሰውነታችንም ጠፋች:: ምድርም ቅልጥማችንን ጠጣች ደም ግባታችንም በመቃብር ጠፋ:: ሥጋችንም በመቃብር ተቀበረ::ያማረ ቃላችንም በመቃብር ታፈነ:: ከሚያምሩ ዓይኖቻችን ትል ወጣ መልካችንም በመቃብር ጠፋ:: ትቢያም ሆነ:: የጎልማሳው ደም ግባት የት አለ:: የአርበኞችስ ጽናት የት አለ? (መቃ ካልዕ ፲፰፡ ፩-፲፬):: እንዳሉት መቃብያን፡- በዚህ አይነት አመራር ውስጥ የሚኖር ዜጋ በመቃብር ውስጥ ያለ ነው:: ሕይወት የተለየው ሬሳ በመሸከም ሰውነታችን እንደ ሰም ቀለጠ፥ አጥንታችንም እንደገል ተቀጠቀጠ:: ሰው መሆናችንም ጠፋ፥ ቅልጥማችንም ተመጠጠ:: የቆየው መሠረታዊው እምነታችን፥ ታሪካችን፥ባሕላችን፥ ክብራችን ዝናችን አቧራ ለበሰ:: ተሰሚነትና ተደማጭነት የነበረው ቃላችንና ድምጻችንተዘጋ፥ የታሪክ የጀግንነትና የሞራል ምንጮች የነበሩት መንደሮቻችንና አምባዎቻችን ሁሉ የትል መፍያ ሆኑ፥ የጎልማስነት ወኔና ሞራል ደብዛው ጠፋ:: የአርበኝነት መንፈሳችን ጠፍቶ፥ በሸፍጠኝነት ተተካ እያሉ ይጮሐሉ:: "በላይሽ ተመመላለስን፣ ለሬሳችን ምንጣፍ ሆንሽ፣ በውስጥሽ ተቀበርን፥ ፍሬሽን በላን፥ አንችም የሰውነታችንን ሥጋ በላሽ" (መቃ ካልዕ ፲፱፡፮-፱):: እያሉ አንገታቸውን ደፍተው ጨካኝና ደም መጣጭ መሪዎችን ያፈራች መሬትን እየቀረቀሩ ጽዋውን የሞላው ግፍና በደል በግፈኞች ላይ የሚደፋበትን ቅጽበት ይጠራሉ:: "ናሁኪ እገሪሆሙ ለእለ ቀበርዎ ለምትኪ ኀበ ኆኅት"(የሐዋ ፭፡፱) እንደተባለውም፥ በእግዚአብሔርና

በሰው በመዋሸት ላይ ያሉትን ሁሉ ለመቅበር የቆሙት ጀግኖች የሚነሡበትን ቅጽበት በመጠበቅ እንቅልፋቸውን ያጣሉ::

“ወለካህናትኒ አግበአሙ ወኀደኀሙ ከመ ያርኩሱ ርእሶሙ ወያኅስሩ ነፍስቶሙ፡ እስከ ይበጽሑ ይትቃተሉ በበይናቲሆሙ በእንተ ኃጢአቶሙ ዘገብሩ በቅድመ እግዚአብሔር” (ቀ.መቃ፲፩፡፲፮):: ካህናት ነን ባዮችም ለጥቅም ለሹመት ሲሉ እርስ በርሳቸው ለግድያ ይፈላለጋሉ:: ሕዝብን ይሸፍጣሉ:: በውስጣቸው ለተዳፈነው ገበና ሽፋኝ መቃብራት በመሆን የተዋረዱና የረከሱ ጠልሰመኞች ይሆናሉ:: የበለስ ቆብ በአጠለቁ እነዚህን በመሰሉ ጠልሰመኞች የሚመራ፥ የሚባረክና የሚሰበክ ሕዝብ እምነትንና እውነትን ለሳቱ የአድመኞችና የቀጣፊዎች መጠቀሚያ ሠራዊት ይሆናል::

ባንድ አካባቢ ከትመው የሚኖሩ ክርስቲያኖች በሌላ አከባቢ ከሚኖሩ ክርስቲያኖች ጋራ በመገናኘት ከካህኑ ከግለ ሰቦችና በመዋቅሩ ባሉት ሰዎች የሚገጥሟቸው ጎጂና ጠቃሚ ነገሮች አለመነጋገር መቃብር ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ “ንትቀኀው ምስለ ቢጽነ በተፋቅሮ ወበምግባረ ሠናይ ወኢንኅድግ ማኅበረነ ዘከመ ይለምዱ ካልአን ዳእሙ ንትገሰጽ እስመ ንሬኢ ዘከመ ትቅረብ ዕለት” (ዕብ ፲፡፳፭):: የዚህ አረፍተ ነገር ቁልፍ ቃላት “ንትቀኀው” እና “ንትገሰጽ” የተባሉት ግሶች ናቸው:: አረፍተ ነገሩ ሲተረጎም፥ በመካከላቸው ችግር ሲፈጠር ችግሩን እየመዘዘን በማውጣት መፍትሔ ለማግኘት እንከራከር እንፋጭ እንወያይ፥ በመካለችን ያለውን ችግር ፈጣሪውንም ያላንዳች ግብዝነት እንገስጽ ማለት ነው::

የሁለት ሺህ ዘመን ታሪክና ልምድ አለኝ የሚል ሕዝበ ክርስቲያን ይቅርና፥ ሁለትና ሶስት አመታት የቆጠሩ ክርስቲያኖች ከያሉበት አጥቢያ እየተሰበሰቡ አስቀድሶና ታቦት አንግሥሶ መበታተን ብቻ የለባቸውም:: የእምነታቸውን መሠረት (ነገረ መለኮት) የጉባዔያቸው መግቢያና መዝጊያ በማድረግ የገጠማቸውን ችግር የመፍታት እምነት መስማማትና ብቃት ሊኖራቸው ይገባል:: ለዚህ ብቃት የሌላቸው ከሆነ፥ ሙዳየ ምጽዋቱን ዘርፎ ለመክበር የሚራወጡ የኔ ቢጤ ካህናት መሳይ እባቦች የሚሽሎከለኩበት የፈረሰ ግንብ ይሆናሉ::

መቃብር ማለት ነፍስ የተለየው በድን የሚቀበርበት ብቻ አይደለም:: የአንዲት አገር ዜጋ በቋንቋና በሃይማኖት ተለያይቶ አትየኝ፥ አልይህ፥ አትስማኝ፥ አልስማህ እየተባባለ እንዲኖርበት ሸፍጥኛ መሪ በዘረጋው መርሆ መፍዘዝና ባዘጋጀው ቀባሪ ሕይወት ተወስኖ መኖር ነው:: ጎን ለጎን ተቀብሮ፥ የፈላበት ምስጥ የሚፈጽምበትን ብሶቱን ልምዱን መለዋወጥ አለመቻል የመቃብር ጎረቤትነት ነው::

ቅዱስ ጳውሎስ “ንቃህ ዘትነውም፡ ወተንስእ እሙታን ወያበርህ ለከ ክርስቶስ”(ኤፌ ፭፡፲፬):: “በቀቢጸ ተስፋ ወድቀህ በማንቀላፋት ላይ ያለህ፥ ከተቀበረው መንፈስህ ተላቀቅ፥ እመን ተስፋ አትቁረጥ የትንሣኤ ብርሃን ምንጭ የሆነው ክርስቶስ በጨለመው ሕይወትህ ያበራልሀል” ብሎ በሰጠው መመሪያ በውስጥም በውጭ ተበትኖ የሚኖረው ሁሉ ኢትዮጵያዊ ዜጋ እንዳይገናኝ በተለያዩ ምክንያቶች ቀብረውና ለያይተው ከያዙት ነገሮች ውስጥ ፈንቅሎ ለመውጣት ወስኖ መነሳት አለበት::

# ፫. ትንሣዔ

"ወምድርሰ ሀለወት እራቃ ወኢታስተርኢ ወኢኮነት ድሉተ ወጽልመት መልዕልተ ቀላይ ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ"(ዘፍ ፩፥፪) በጥልቁ ጨለማ የነበረች ዓለም፥ ሕይወት ለማመንጨት የእግዚአብሔር መንፈስ በውሀው ላይ እንደንዣበበ፥ "ናሁ ይመጽእ በደመና ሰማይ ወትሬእዮ ኵሎ ዓይን"(ራዕ ፩፥፯):: ክርስቶስም ሙታንንን ለማንሣት በሕይወት ሰጭና ሙታንን በሚቀሰቅስ ደመና አንዣቦ ይመጣል:: "ወመጻት ደመና ብርህት ወውስተ ደመና ይነብር ወልደ እጓለ እመሕያው"(ራዕይ ፲፬፥፲፬):::: እንዲል ክርስቶስ የሚመጣበት ደመና አፈር ትቢያ የሆነውን የሰውን አካል ለመቀሰቅስ መለኮታዊ ኃይል አለው ይሉና፥ ከባሕርና ከቀላይ የሚነሣው ደመና አፈር ትቢያ የሆነውን ሰርዶ የሚያለመልም፥ የነበሩበት ውኀ ሲደርቅ ወደ አፈርነት የተለወጡትን እንቁራሪቶች የሚቀሰቅስ ከሆነ፥ ክርስቶስ ተጭኖ የሚመጣበት ደመና አፈር ትቢያ የሆነውን ሰብአዊ አካል ቀስቅሶ ማስነሣት መቻሉን መጠራጠር እንደሌለብን ሊቃውንት ይናገራሉ::

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት አበው እነ ኤጲፋንዮስ ስለ ትንሣኤ ሲናገሩ፥ በደመና የሚንቀሳቀሱትን ተሐዋስያንና አዝርእቶችን እንደምሳሌ ጠቅሰዋል:: "ወአንበጣሂ እምድኅረ ሞተ ይትነሣእ እምነ ምድር:: እምልደት ዘወጽአ እምኔሁ:: ወፍሬያትሂ ይዘርው ወይመውቱ ቅድመ ውስተ ምድር:: ወእምድኅረ ዘመን ታወጽእ ምድር ዘቀበረት ውስቴታ ወለእመሂ ኢሞቱ ኢየሐይው" (ሃይ ምዕ ፶፰፥፯) ብለዋል:: ይህም ማለት በወቅቱ የሕይወት ደመና በመሬት ላይ ሲያንዣብብ የሞተው የበሰበሰው አንበጣ ከምድር እንደሚፈላ፥ ክርስቶስ በደመና ተጭኖ ሲመጣ አፈር ትቢያ ሆኖ እባቡ ሲልሰው የነበረው ሁሉ ሰባዊ አካል ከምድር ይነሣል::

ከክርስትና በፊት "መቃብራችሁን እከፍታለሁ:: ከመቃብራችሁም አወጣችኋለሁ" (ሕዝ ፴፯፥፲፪):: እየተባለ በነብያት ሲነገር ኖሯል:: ከነብያት ወዲህ ክርስቶስ ሊወለድ አቅራቢያ "የሚሞቱ ሰዎች መነሳታቸውን ካላመንክ ከእናት ከአባታቸው ሳይወለዱ በክረምት ከየቦታው የሚፈሉትን ፍጥረታት ተመልከት"(ሣል መቃ ፲፥፩):: እየተባለ ስለ ሰው ልጅ ትንሣዔ በተለያዩ ምሳሌዎች ተደጋግሞ ተነግሯል:: "የስንዴም ሆነ የገብስ ሌሎችም በምድር የሚዘሩት ሁሉ ቅንጣት ካልሞቱና ካልበሰበሱ አይበቅሉም"(ቀዳ መቃ ፰፥፳፪) እየተባለ ተገልጿል:: ጊዜው ሲደርስ "እውነት እውነት እላችኋለሁ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች:: ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች" (ዮሐ ፲፪፥፳፬):: እያለ የሕይወት ባለቤት ክርስቶስ ስለትንሣዔ መኖር አረጋገጠ:: ጊዜው ደርሶ ክርስቶስ ሞትን ድል ነሥቶ የተናገረው የመጀመሪያ ቃሉ "ተውህበ ሊተ ኵሉ ኵነኔ ሰማይ ወምድር"(ማቴ ፳፰፥፲፰):: የሚል ነው:: ማለትም፡- በሰማይና በምድር ስልጣን በእጄ ገባ ብሎ ነው::

ቅዱስ ጳውሎስም፥ "አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም"( ፩ኛ ቆር ፲፭፥፴፮):: እያለ አጠንክሮና አረጋግጦ ስለትንሣዔ ያስተማረው ከዚህ ተነሥቶ ነው:: በመቀጠልም ቅዱስ ጳውሎስ "ወእምዝ ይሰአር ደኀሪ ጸላኢ ዘውእቱ ሞት"(፩ኛ ቆሮ ፲፭፥፳፮):: እያለ አጠንክሮና አስረግጦ አስተማረ:: ማለትም፡-ከእንግዲህ ወዲህ ጠላታችን ሞት ተሽሯል:: "ዘይሔድስ ሥጋነ ትሑተ ወይሬስዮ አምሳለ ሥጋ ስብሐቲሁ በከመ ረድኤቱ"(ፊል ፫፥፳፩):: በመሬትና በእባቡ ላይ የተሰነዘረው መርገም ተፈጸመ:: በሰው ላይ የተሰነዘረው የሩቅ ዘመን የመቃብር ቆይታ ከወደቅንበት ለማንሣት በነበረው እቅዱ በትንሣዔው ኃይል አድሶ ያነሣን ዘንድ ለትንሣዔያችን በኩር ሆነን:: እያለ ሰበከ::

ክርስቶስ ስልጣን ተሰጠኝ ብሎ የተናገረውን፥ ሐዋርያት በሰፊው ካስተጋቡት አዋጅ በመንደርደር፥ የነገረ መለኮት እውቀት መሠረቶች ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ወበከመ ከይሲ ዘኮነ ያመልክዎ ሰብአ ባቢሎን ሶበ ውህጠ መብልዐ ዘመጠዎ ነቢይ ተሠጥቀ እማእከሉ ከማሁ ተሰጥቀ ሞት ሶበ ውህጠ ሥጋሁ ለእግዚእ፥ ወሶበ ውህጠ ውእተ ሥጋ ቅዱሰ ሠጠቀ ከርሶ ወተንሥአ እሙታን ሕያወ" (ሃ.አ. ፷፯፡ ፲፷)፡፡ በማለት የሰው አቅም በሚረዳላቸው በተለያዩ ምሳሌዎች እያረጋገጡ አስተማሩት፡፡ ማለትም የባቢሎን ዘንዶ ዳንኤል ያዘጋጀውን ሥጋ በዋጠ ጊዜ፥ እንደ ሌላው ሰው አካል የሚውጠው መስሎት፥ የጌታን ሥጋ ውጦ መቃብር ተሰነጠቀ ሞትም እንደ ዘንዶው ፈነዳ፡፡ በእባብና በሰው መካከል የነበረው ዘላለማዊ የተበይና የበይነት ግንኙነት ፈረሰ፡፡ እባቡ በደረቱ ለዘላለም ይሳብበትና ይንከባልለበት ዘንድ ሰው ዘላለማዊ አፈር ትቢያ መሆን ቀረለት፡፡

ይሁን እንጅ አሁን ባለንበት ምድር በጊዜያዊ ሁኔታችን ስላለን፥ ሰይጣን በእባቡ አካል ተሰውሮ፥ አፈር የሆነውን አካል እንደሚልሰውና በደረቱ እንደሚሳብበት፥ በሸፍጠኞች ሰዎችም ተሰውሮ እንድንላስ እንድንበላ ከማድረግ አይመለስምና ከዚህ አይነት ሕይወት ራሳችንን አድነን ሌላውም ከዚህ አይነት ሕይወት እንዲድን ምስክር ለመሆን ተጠርተናል፡፡

# ፬. ምስክሩ ማን ነው?

ስለ ሞት መቃብርና ትንሳኤ ማን ይናገር? ምስክሩስ ማነው? ለሚለው ጥያቄ "ማን ያርዳ የቀበረ፡ ማን ይናገር የነበረ" የሚለው አነጋገራችን የመለሰው ይመስላል፡፡ ይሁን እንጅ ማነው የሞተ የተቀበረ? መመስከር የሚችለውስ የቀበረና ያየ ማነው? ዛሬ አገራችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን የገጠሟቸው ችግሮች ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ማጣታችን ነው፡፡

ስለ ክርስቶስ መሞት መቀበርና መነሳት ለመመስከር ኃላፊነት ያለባቸው፥ ቅዱስ ጳውሎስ "ሥጋውን በምትበሉበት ደሙን በምትጠጡበት ጊዜ ጌታ እስኪመጣ ትናገራላችሁ"(፩ኛ ቆሮ ፲፩፡፳፮) ብሎ እንደተናገረው፥ አምነው ተጠምቀው "ሞትህን ቅድስት ትንዋዔህን እርገትህን ዳግም መምጣትህን እንናገራለን"(ሥቅ፡ ገጽ ፺፩፡ ፵፮)፡፡ እያሉ ሥጋውንና ደሙን የሚቀበሉ ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡ የምስክርነቱን ኃላፊነት ምእመናን እንዳይዘነጉ የሚያሳስቧቸው የሚያንጿቸውና የሚያበረታቷቸው ቀሳውስት ነበሯቸው፡፡ ቀሳውስቱ "እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንንም እናካፍላችሁ ዘንድ ፈቃዳችን ነበረ ለኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበረና"(፩ኛ ተሰ ፪፡ ፰)፡፡ በማለት ምእመናን በመንፈስ፥ በእምነት፥ በፍቅር፥ በነጻነትና በኅብረት በሰላም እንዳይኖሩ ለሚያደርግ መስዋዕትነት ለሚያስከፍል ነገር ሁሉ ኃላፊነት የተዘጋጁ መሆን ነበረባቸው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሐዋርያት ሥራ ምዕ ፲፩ ላይ የሰፈረውን ታሪክ መነሻ አድርጎ እንደመዘገበው፥ ለሕዝበ ክርስቲያን መጎዳት ምስክር ለመሆን እጽፍ ድርብ ሐላፊነቱ የወደቀባቸው በሚሊጢንና በኤፌሶን የነበሩ በትዳር የተወሰኑ ቀሳውስት ነበሩ፡፡ ከጊዜ በኋላ "ሚስቱን ልጁን ያልተዎ ለኔ ሊሆን አይገባውም" የሚለውን የክርስቶስ ትእዛዝ ወደ ኋላ ገሸሽ አድርገው ለትዳራቸው ቅድሚያ በመስጠት፥ ከምእመናን የሚሰበሰበውን ሙዳየ-ምጿት ወደግል ንብረትነት እየለወጡ ከቀራጮችና ከነጋዴዎች ጋራ እኩል ለመኖር መወዳደሪያ ያደረጉ ቀሳውስት ተከሰቱ፡፡ ከድሖች የሚሰበሰበውን ሙዳየ ምጿት ሚስቶቻቸውን ከሌሎች ሴቶች በላይ አድርገው አስጌጡበት፥

ልጆቻቸውን ከምእመናኑ ልጆች የበለጡ ከዋክብት አደረጉበት:: ሕይወታቸውን ከተራው ምእመናን በላይ እጅግ አጓኑ፥ ሕዝቡን የሚዘርፉትን የሚበዘብዙትን ሰዎች ከመቃወም ይልቅ ተባበሩ::

ይህ አይነት ሰባዊ ባሕርይ ባንዳንድ ካህናት ላይ መከሰቱን አስቀድሞ የተረዳው ቅዱስ ጳውሎስ "ያገባ ሰው ልቡ በትዳሩ በመከፈሉ የዚህን ዓለም ነገር ያስባል" (፩ና ቆሮ ፯፡፴፫) ብሎ ተናገረ:: ቅዱስ ጳውሎስ የፈራው አልቀረም:: "ለምታገለግሉት መንጋ ተጠንቀቁ"( የሐዋ ፳፡፳፰) የሚለውን ክህነታዊ አደራ ሊፈጽሙ ይቅርና ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መመስከሩን የረሱ ካህናት ተፈጠሩ:: ሰአታቸውን ለሕዝብ አገልግሎት ሊሰጡ ቀርቶ፥ የቤተ ክርስቲያኑን ንብረት ሁሉ በስማቸው በማዞር ለራሳቸው ቤተ ሰብ ጥቅም ላይ ብቻ አዋሉት::

ከዚህ አይነት ችግር ለመላቀቅ ሲባል ብቻ "ዓለም ለኔ ከተሰቀለበት እኔም ለዓለም ከተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ መስቀል በቀር ሌላው ትምክህት ከእኔ ይራቅ"( ገላ ፮፡፲፬) ብለው በመጀመሪያ ፈጣሪ ከደነገገው ሕገተፈጥሮ፥ ክርስቶስ ከቀደሰው ጋብቻ ሳይቀር ራሳቸው የለዩ የገደሉና በበርሀ የቀበሩ መነኮሳት የቤተ ክርስቲያን የበላይ ተመልካቾች እንዲሆኑ ከጊዜ በኋላ ተወሰነ:: እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂዎች ያላገቡ እንዲሆኑ የተደነገገው ምንኩስና በሕገ-ፍጥረት ከተሠራውና ክርስቶስም ከቀደሰው ጋብቻ የበለጠ ቅዱስ ሳይሆን፥ ሐላፊነታቸውን በረሱ፥ ምእመናንን ከሚጎዱ ጋራ በተባበሩት ስግብግብ ቀሳውስት ስሕተት ምክንያት መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል::

ከክርስቶስ ጋራ በጥምቀት መቀበርንና መነሣትን የምስክርነት ኃላፊነት በክርስትና ሃይማኖት አምኖ የተጠመቀ ሁሉ የሚካፈለው የውዴታ ግዴታ ቢሆንም፥ የምስክርነቱ ተልእኮ "ያላገባ ሰው ጌታን ደስ ለማሰኘት ስለ ጌታ ነገር ያስባል" እንደተባለው፥ የሲኖዶስ አባላት ያላገቡ እንዲሆኑ በኋላ የተደነገገው፥ ስለ ጌታ ነገር ብቻ እያሰቡ ጌታን ማስደሰት የሚችሉ እንዲሆኑ ነበር::

ያላገቡ የሲኖዶስ አባላት የሚያስቡትና የሚጨነቁት ስለ ጌታ ነገሮች ብቻ እንዲሆንነበር ከተባለ፥ ይህ ሊጨነቁለት የሚገባ የጌታ ነገር ምንድነው? የሚል ጥያቄ መፍጠሩ አይቀርም:: የጌታ ነገር የተባሉት ለጌታ ፍቅር መለኪያና መግለጫ የሆኑት የተሰቀለላቸው የሞተላቸውና በኋላም በትንሣኤው የዘላለም ሕይወት የከፈተላቸው ጠቦቶቹ በጎቹ የሚላቸው ክርስቲያኖች ናቸው::

ቤተ ክርስቲያናችን እነዚህን የክርስቶስ ነገሮች የተባሉትን የመነኑ የሞቱ የተቀበሩ እንዲጠብቁ የተሠራውን ሥርአት ከተቀበሉት አብያተ ክርስቲናት አንዷ በመሆን፥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፥ ቁጥራቸው ከሐዋርያት ቁጥር ያልበለጡ አካቶ የያዘ በምንኩስና ላይ የተመሠረተ ሲኖዶስ ነበረን:: በትዳር ያልታሰሩ፥ የግል ንብረትና በሥጋ ዘመድ ከመከበብ የራቁ፥ በሴት የማይታሙ በመንፈስ በሞራል በእውቀት ልዑላን ብፁዐን ነበሩ:: ለአገልግሎት ከሕዝብ ጨርሰው እንዳይርቁ በከተማ ቢኖሩም፥ ብዙውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ኢትዮጵያዊውን ነገረ መለኮትና ሥነ ልቡና ለማጤን በገዳምና በመቃብር ቤት ነበር:: በአጭሩ "እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንንም እናካፍላችሁ ዘንድ ፈቃዳችን ነበረ ለኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበረና"(፩ኛ ተሰ ፪፡፰) የሚለውን ህይወት ለመኖር ሳያሰልስሱ ይጥሩ ነበር::

ዛሬ የተቀደሰው ሥርአት ፈረሰና፥ የዘመናችን መነኮሳት፥ ከዘመናችን ፓትርያርክ ጵጵስናውን ለመግዛት ብዙ ሺ ብር ይዘው ቀረቡ:: ይህም ሰሞኑን በየድኅረ ገጹ በሰፊው ተገለጠ:: ሰው ከገዛበት ዋጋ እጥፍ የሚያተርፍበትን እንጅ፥ የሚያከስረውን አይገዛም:: የምንኩስናና የጵጵስና ትርጉም ካልተለወጠ በቀር፥ ጵጵስና

ማለት ተላልፎ ለመሞት ነው:: ታዲያ ጵጵስናውን በመሸጥና በመግዛት ላይ ያሉት ሰዎች ለሕዝብ አስበው ለሕዝብ ፍቅር ሲል ሞት ሸጥኩ፥ ሞት ገዛሁ ሊሉ ይችላሉን?

በዚህ አይነት ጳጳሳት የሆኑ የገዘቡትን ዋጋ በእጽፍ ድርብ ለማስመለስ ገንዘብ ባለበት ቦታ ለመድረስ በዓለም ዙሪያ እየፈረጠጡ ከመራወጥ በቀር "እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንንም እናካፍላችሁ ዘንድ ፈቃዳችን ነበረ ለኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበረና"(፩ኛ ተሰ ፪፡፰):: በማለት መሞትን መቀበርንና መነሳትን በምን ሞራላቸው ሊመሰክሩና ሊነግሩ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ይፈጥራል

ያም ሆነ ይህ በዚህ ዘመን በአገር ውስጥና ውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ሁላችን ቁሱም ጳጳሱም ሕዝበ ክርስቲያኑም በየተሰለፍንበት መስመር የሚጠበቅብንን ኃላፊነት ሳንወጣ ቀርተን፥ "አፈር ብላ" በሚለው ተስፋ አስቆራጭ ባሕላዊ መርገም እንዳንወድቅ ለማሳሰብ ይህችን ጦማር "አፈር ብላ" በሚለው አንቀጽ እደመድማለሁ::

# ፭. "አፈር ብላ"

በባሕላችን ጸያፍ የስድብ ቃል አልነበረንም:: ኢትዮጵያውያን፥ ምክር የማይሰማ ሰው በመካከላቸው ሲከሰት፥ ከምትንከባለልበት አመድና ከምትግጠው ሣር በቀር ምንም ከማታስታውሰው እንስሳ ጋር በማነጻጸር አህያ ነህ ይሉታል፥ በሚላስና በሚቀመስ ቀላል ነገር የሚታለል ከሆነ ደግሞ ውሻ ነህ ይሉታል:: ሥልጣኑን ተገን አርጎ እየዋሸ እየቀጠፈ ህዝብ የሚዘርፈውን የቀን ወይም የጉም ጅብ ነህ ይሉታል:: ከዚህ ሁሉ በከፋ ተግባሩ ኅብረተ ሰቡን የሚያስመርር ሰው ሲከሰት፥ "አፈር ብላ" ይሉታል:: በአንቀጽ ተራ ቁጥር ፩ ላይ እንደገለጽኩት ይህ አፈር ብላ የሚለው ኢትዮጵያዊ ተግሳጽ የመነጨው፥ ሰው የገነትን ፍሬ ቀጥፎ ከበላ በኋላ ቆርጦ በተደበቀባት በለስ ከፈጣሪው ለመደበቅ ሲሞክር ከፈጣሪ የተሰነዘረበት የቅጥፈቱ ፍዳ ነው::

ፈጣሪያችንን ለማምለክ ወደ ቤተ መቅደስ ስንገባ "ዘአንሣእከነ እምድር ወአልዐልከነ እመሬት ከመ ታንብረነ ምስለ መላእክቲከ ወምስለ መላእክተ ሕዝብከ"(ሥ. ቅ ገጽ ፴፡፳፩):: በማለት እየሰገድን ቅዳሴውን እንድንጀምር የአምልኮታችን መመሪያ ያዝዘናል:: ይህም "መጀመሪያ በአርያህና በአምሳልህ ሰው አርገህ ከመሬት አፈር የፈጠርከን፥ ቀጥፈን ባመጣነው ፍዳ ሞተን ከተቀበርንበት በትንሣኤ አንሥተህ ከቅዱሳንና ከመላእክት ጋራ ከብረን ለዘላለም እንኖር ዘንድ የትንሣኤን እቅድ ዘረጋህልን" የሚል ነው:: ይህ ሥርአት "አፈር ብላ" ተብሎ በእባቡ፥ "አፈር ሁን" ተብሎ በሰው ላይ የተሰነዘረውን አምላካዊ ተግሳጽ የሚያመለክት ነው:: የፈጣሪን ኃያልነትንና ቸርነትን፥ የሰውን ፍጡርነትንና ደካማነትንም የሚገልጽ ነው::

በቤተ ክርስቲያናችን ነገረ መለኮት ረቀውና መጥቀው የላቁት አበው፥ እኩለ ቀን ሆኖ አካባቢው ጸጥ ሲል፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ካንዱ ዛፍ ስር ሆነው ይህን ከላይ የጠቀስኩትን ቃል እየመላለሱ ካፋቸው በማውጣት የአምላካቸውን ኃያልነትና የራሳቸውን አፈር ትቢያ መሆን ላአምላካቸው በስግደት ካቀረቡ በኋላ፥ በተጠጉባት ዛፍ ጥላ ሥር ቁጭ ብለው ተፈጥሮን ማሰላሰል ይጀምራሉ::

እደሚታወቀው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን የሸፈኑት ዛፎች ሥሮቻቸውን አሰራጭተው የበቀሉት በኢትዮጵያውያን መቃብር ላይ ነው:: በቀጥሎቻቸው አማካይነት ከጸሐይ ብርሃን ከሚያገኙት ንጥረ ነገር በቀር፥ መላ አካላቸው የተሸከመውና የተገነባበት ንጥረ-ነገር ለብዙ ዘመን እየተደራረበ የተቀበረው የኢትዮጵያውያን አካል ነው:: ሊቃውንት አበው በነዚህ ዛፎች ጥላ ስር አርፈው ባካባቢው ያለውን የተፈጥሮ ትርምስ በተመስጦ ይመለከታሉ:: እባቦች ከአፈር ጋራ የተቀላቀለውን የሰውን አካል ሲልሱ፥ በደረታቸውም ሲሳቡበት በአንክሮ ያያሉ:: በዛፉ ላይ የሰፈሩ ወፎችም አፈር በመላስ ላይ ያሉትን እባቦች እያዩ ሲንጫጩ ይሰማሉ:: አፈር ትቢያ በሆነው አካልና፥ በመላስ ላይ ባሉት እባቦች፥ የወፎችንም ጫጫታ ባንድምታ ትርጓሜ ምሥጢር በታሸው አዕምሯቸው አገናዝበው ያመሠጥሩታል:: እንደ እባቡ 'የሚልስ' እንደ አፈሩ 'የሚላስ' እንደ ወፎችም የሚንጫጫ ዜጋ ባካባቢያቸው መኖርና አለመኖሩን ይፈትሹበታል::

"እበያ ለፍትወተ ዝንቱ ዓለም ለእመ ፈቀድከ ከመ ትርከብ ፍስሐ ወሐሴት በዘትመጽእ ዓለም"(መቃ ሣልስ ፲፡፳፱):: እንዲል ሰው ከትንሣዔው በኋላ በምትመጣው ዓለም የሚገኘውን ዘላለመዊ ደስታ ለማግኘት፥ ቀጣፊውን አፈር ብላ በማለት መተባበር እንዳለበት ይገነዘባሉ:: አፈር ብላ መባል የሚገባውን ሰው ለማለት የማይደፍር ሰው፥ በፍርሐት የተሞላ ነው:: ፍርሐት ደግሞ ከሞራል ከጽድቅና ከእምነት ተራቁቶ በተቀጠፈችው በለስ ለመደበቅ መሞከር ነው:: ትጋርደኛለች ብሎ የሚያዘጋጃት የበለስ ቅጠልም ወደ ዘላለማዊ መቃብርነት እንደምትለውጥበትም ያያሉ:: የጥንቷ ኢትዮጵያዊነት አስኳል ይህ ነበር::

ሰይጣን የሚጠቀምበት እባብ ሳያዩት ተደብቆ ይነድፋል፥ ይልሳል:: ሲያዩት ደግሞ መሬት ሰንጥቆም ቢሆን ለማምለጥ ይሞክራል:: በዚህ አይነት መንፈስ የተቃኙ መሪዎች እንደ እባቡ አገር ድንበር ባህል ታሪክ አንድነት እየሰነጠቁ ይገባሉ:: እባብ ሆኖ መሬት ሰንጥቆ መግባትም ሆነ፥ መሬት ሆኖ በእባብ መሰንጠቅ ሰው ራሱ በሸፍጡ ያመጣው የመርገም ውጤት ነው:: ቢሆንም ሰው የሆነ ሁሉ ሰው በመተባበር፥ ቅዱስ ጳውሎስ "አምላከ ሰላም ለይቀጥቅጦ ለሰይጣን በታሕተ እገሪክሙ ፍጡነ"(ሮሜ ፲፮፡፳):: ሲል ባሰማው መፈክር እየተመራ፥ ከእግዲህ ወዲህ አፈር ትቢያ ሆነን እንዲልሰን ለእባቡ አንፈቅድለትም ማለት አለበት::

የፋሲካው (ትንሣዔው) በዓል ያዘለው መልእክት፥ "ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ" እያልን የምንዘምረው አመታዊ መዝሙራችን የተሸከመው ምሥጢር ነው::ሊቃውንት አበው አመሥጥረው መተርጎም ባሳዩን መንገድ ይህ አመታዊ መዝሙር ሲተረጎም "የፋሲካውን በዓል የምናከብረው አፈር ትቢያ ሆነን በእባቡ ስንላስ፡ ስንቀመስና ስንበላ የነበርን ሰዎች ብቻ አይደለንም፥ የሚልሱን እባቦችም እኛን መላሳቸውን አቁመው፥ ቁስላችንን እየጫሩ የሚያደሙንም ዝምቦች እኛን ማድማታቸውን አቁመው የፋሲካውን በዓል በማክበር ይተባበሩ" ማለት ነው::

በተረፈ፥ አፈር ትቢያ ሆነን በእባቡ እየተላስን፥ መንከባልያም ሆነን ከመኖር ያውጣን:: እባቡም አፈር ከሆነው ሰብአዊ ሰውነት እየላሰ ከመኖር፥ መንከባለያውም እንዲያደርግ ከገባበት መርገም ተላቆ፥ በደረቱ መሳቡንም አቁሞ፥ በእግሩ ቀጥ ብሎ እንዲቆም ያደርገው ዘንድ የፋሲካው በዓል ማዕከል የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይርዳን::

ይቆየን